# ዓለም አቀፍ የመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ተቋም

# ዓ. መ. ጤ. አ. ተ

**በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ አማካኝት**
**ጤና ለሁሉም!**

## ዓለም አቀፍ
## የመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ተቋም
## ዓ. መ. ጤ. አ. ተ

ዓ. መ. ጤ. አ. ተ በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ስልጠናዎች እና ምርምሮችን የሚያካሂድ ዓለም አቀፋዊ የልህቅ ማእከል ሲሆን ይህ ተቋም የተመሠረተውም በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ አማካኝነት ጤና ለሁሉም የሚለውን ዓለምአቀፋዊ እንቅስቃሴ የማነቃቃት ድርሻን እንዲወጣ ለማስቻል ነው።

ዓ. መ. ጤ. አ. ተ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ስልጠና በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ላይ ከአፍሪካ እና ከሌሎች የአለም ክፍል ለተውጣጡ ተሳታፊዎች ስልጠና የሚሰጥ ተቋም ነው።

ይህ ተቋም የመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ላይ ወቅታዊ መረጃዎች የሚሰጥ ከመሆኑም በተጨማሪ ቀጣይነት ባለው መልኩ ጠንካራ የመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም እንዲኖር አስተዋፆ ያደርጋል። ይህም በመሆኑ ሀገሪቱ የላቀ ደረጃ ያለው የጤና አገልግሎት ተጠቃሚ እንድትሆን ያስችላታል።



ከዚህ በተጨማሪ ይህ ተቋም በመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ዙሪያ ያሉ የውስጣዉ አሠራር ሂደቶችና የአመራር ዘዴዎችን እንዲጠናከሩ ያደርጋል።

የስልጠና መርሀግብሮች በኢትዮጵያ የካበቱ ልምዶች እና በመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ የፈጠራ ስራዎችን በያዙ ምርጥ ተግባራት እንዲሁም በየደረጃው የሚሰጡ ህብረተሰባዊ ተኮር የጤና ፕሮግራችን የታገዙ ነው።

## 1 ራዕይ

**ራዕያችን በመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ዙሪያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው የእውቀት ማእከል ሆኖ ማየት።**



# ጤና ለሁሉም

## 2 ተልዕኮ

**በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ዙሪያ ያሉ አዳዲስ የአሰራር ስልቶች አና መረጃዎች መሠረት ያደረገ ስልጠና እና ምርምር ማካሄድ እንዲሁም የመረጃ ማእከል በማቋቋም ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ማበርታት፤**

**ዓ. መ. ጤ. አ. ተ የሚከተሉትን ቁልፍ ተግባራት ያከናውናል**

1. ለፖሊሲ አውጪዎች፣ ለጤና ፕሮግራም ቀያሾች፣ እንዲሁም ለመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ፕሮግራም አስፈፃሚዎች የቴክኒክ እና የአመራር ብቃታቸውን ማሳደግ።
2. በመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ዙሪያ እና ህብረተሰብ ተኮር የሆኑ የጤና አገልግሎት ላይ የፈጠራ አሰራሮችን መንደፍ።
3. በመሠረታዊ የጤና አጠባበቅ ዙሪያ ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ጥናቶችን ማከናወን።

## 3 የዓ. መ. ጤ. አ. ተ ተግባራት

- በተመረጡ ፍላጎቶች ላይ የተመሠረቱ በሀገር ውስጥ ላሉ እና በዓለም ዓቀፍ ከሌሎች ሀገሮች ለሚመጡ ሠለጣኞች አጠር ያሉ የአቅም ግንባታ ስልጠና የሚሰጥ ሲሆን፣ ይህም ስልጠና መሠረታዊ ጤና አጠባበቅ እና ህብረተሰብ ተኮር ዙሪያ መርሀግብሮችን ለመቅረጽ እና ለማጠናከር ያስችላል።
- በመሠረታዊ እና በህብረተሰብ ተኮር ጤና አጠባበቅ ላይ ለሚገኙ ሀላፊዎች በሥራ ሂደትና በአመራር ስርዓት ዙሪያ አጫጭር ስልጠናዎችንና ድጋፍ ይሰጣል።
- መንግስት ባወጣው የጤና ዘርፍ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅድን መሠረት የደረገ የአጭር ጊዜ ስልጠና ያካሄዳል።
- ፍላጐት መሠረት ያደረገ መሠረታዊ ጤና አጠባበቅ እና ሕብረተሰብ ተኮር የሆኑ ፐሮግራሞች ላይ ጥናት እና ምርምር ያካሄዳል።
- በኢትዮጵያ ውስጥ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ለክልል ጤና ቢሮዎች እንዲሁም በሀገር ውስጥ አና ከሀገር ውጪ ለሚገኙ ሌሎች ተቋማት የመረጃ ማዕከል በመሆን ያገለግላል።
- በመሠረታዊ እና በህብረተሰብ ተኮር ጤና አጠባበቅ ላይ ያሉ የፖሊሲ ለውጦች፣ የምርምር ግኝቶችንና ሌሎች ወቅታዉ ሁኔታዎች ላይ ዓውደ ጥናት ያዘጋጃል።
- በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ዙሪያ የተለያዩ ጥናቶችን የሚያሰባስብ እና የሚያቀርብ ዓለም ዓቀፍ መፅሄት ያቋቋማል።
- የሀገሪቷ ዋና የመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ ተቋም ለመጐብኘት ከተለያዩ የአፍሪካ እና ሌሎች አህጉራት ለሚመጡ እንግዶች በመቀበል አስፈላጊውን መስተንግዶ ያደርጋል።

## 4 ስልጠና

- አጠቃላይ ስለሀገሪቱ ያሉ መረጃዎች የጤና ፖሊሲ እቅዶችን የጤናውን ዘርፍ የገንዘብ አስተደደር እንዲሁም ክትትል እና ግምገማን በማስመልከት አጠር ያለ ገለፃ ያደርጋል።
- በመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ እና በጤና ኤክስቴንሽን ፐሮግራም አፈፃፀም አስመልክቶ በክፍል ውስጥ ስልጠና ይሰጣል።
- ለተለያዩ ሰልጣኞች ተሞክሮን መሰረት ያደረግ ስልጠና ይሰጣል።
- ሀገሪቱ ከጤና ኤክስቴንሽን ፐሮግራም እና ከጤና ልማት ቡድን የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች ለማሳየት የመስክ ጉብኝት ለሰልጣኞቹ ያመቻቻል፤ እንደሁም ሞዴል ተብለው የተመረጡ ቤተሰቦች በመስክ ጉብኝት ያካፍላል።
- ሰልጣኞች ትምህርታቸውን በተመለከተ ድጋፍ ሰጪ የሆኑ የተለያዩ ማኑዋሎች መመሪያዎችን እና የስልጠና መፀሀፎችን በCD ወይም በፍላሽ ተዘጋጅተው ይሰጣቸዋል።



## 5 ወቅታዊ የስልጠና መርሀግብር

**ፖሊሲ ቀራጮች (የ3 ቀን ስልጠና)**

ለፓርላማ አባሎች ለጤና ሚኒስቴሮች ለህግ ባለሙያዎች፣ ለጤና እና ለኢኮኖሚ አማካሪዎች ያካትታል።

**የጤና ፐሮግራም ቀያሾች (የ2 ሳምንት ስልጠና)**

በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በክልል እና በዞን ጤና መሪዎችና ሀላፊዎች ያጠቃልላል።

**የመሠረታዊ ጤና አጠባበቅ አስፈጻሚዎች (የ6 ሳምንት ስልጠና)**

በወረዳ እና በጤና ጣቢያ ያሉ ሀላፊዎች እና ባለሙያዎችን ያካትታል።

## 6 ለመሳተፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

በተቋሙ የሚካሄዱት የስልጠና እና የምርምር ስራዎች ላይ ለመሳተፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ይመልከቱ።

- በስልጠናም ሆነ ለምርምር ላይ መሳተፍ ሲፈልጉ ተቋሙን በትንሹ ከስድስት ሳምንት በፊት ጥያቄዎን ማስታወቅ ያስፈልጋል።
- ክፍያው የቀናት ብዛት እና የስልጠናው ዓየነትን መሠረት አድርጐ ስለሆነ ይለያያል።
- የስልጠናውን በግላቸው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ወጪያቸውን ሸፍነው መሳተፍ ይችላሉ።

**ለበለጠ መረጃ እባክዎን የግንኙነት የስራ ባልደረባችን የሆኑትን ወ/ሮ ልዊዲና ኃይሉ በሚከተሉት አድራሻዎች አግኝተው ያነጋግሩ**

+ 251 912 623 836;
+ 251 929 951 092

luidina@iifphc.org

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Health

Ethiopian Public Health Institute
www.iifphc.org

JOHNS HOPKINS BLOOMBERG SCHOOL of PUBLIC HEALTH